# 3ኛ የዮሐንስ መልእክት

፩ ሽማግሌው በእውነት እኔ ለምወደው ለተወደደው
ለጋይዮስ። ፪ ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ
እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ። ፫ ወንድሞች
መጥተው አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ
እጅግ ደስ ብሎኛልና። ፬ ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት
ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም። ፭ ወዳጅ ሆይ፥ ምንም
እንግዶች ቢሆኑ፥ ለወንድሞች በምታደርገው ሁሉ የታመነ ሥራ
ትሠራለህ፥ እነርሱም በማኅበር ፊት ስለ ፍቅርህ መሰክረዋል፤
፮ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው ብትረዳ
መልካም ታደርጋለህ፤ ፯ ከአሕዛብ አንዳች ሳይቀበሉ ስለ ስሙ
ወጥተዋልና። ፰ እንግዲህ ከእውነት ጋር አብረን እንድንሠራ
እኛ እንዲህ ያሉትን በእንግድነት ልንቀበል ይገባናል። ፱ ወደ
ቤተ ክርስቲያን ጻፍሁ፤ ዳሩ ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ
ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም። ፲ ስለዚህ፥ እኔ ብመጣ፥ በእኛ
ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ሥራውን አሳስባለሁ፤
ይህም ሳይበቃው እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም፥
ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተ ክርስቲያን
ያወጣቸዋል። ፲፩ ወዳጅ ሆይ፥ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን
አትምሰል። በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፤ ክፉን
የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም። ፲፪ ለድሜጥሮስ
ሁሉ ይመሰክሩለታል፥ እውነት ራሰዋም ትመሰክርለታለች፤ እኛም
ደግሞ እንመሰክርለታለን፥ ምስክርነታችንም እውነት እንደ ሆነ
ታውቃላችሁ። ፲፫-፲፬ ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ፥
ዳሩ ግን በቀለምና በብርዕ ልጽፍልህ አልወድም፤

# መጽሐፍ ቅዱስ
# The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

copyright © 1962, 2003 United Bible Societies

Language: አማርኛ (Amharic)

**Amharic NT**

Revised Amharic Bible in XML (2003).

Printed version by United Bible Societies (C)1962.

E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994.

Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net).

With kind permission of the Bible Society of Ethiopia.

Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement!

Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

2014-09-09

---

PDF generated using Haiola and XeLaTeX on 11 Nov 2022 from source files dated 9 Oct 2020
2432e07d-4260-5d76-afcb-ce35bd1c48b7